# 279/2013

## መግቢያ

ሀገራችን ከማዕድን ዘርፉ የውጭ ምንዛሪ ከምታገኝባቸው መንገዶች አንዱ የከበሩና በከፊል የከበሩ ጌጣጌጥ ማዕድናት ለውጭ ገበያ እንዲቀርቡ በማድረግ ነው። ግብይቱም የሚሳለጠው በላኪዎችና በዕደ ጥበብ /የላፒደሪና የስሚዘሪ/ ባለፈቃዶች በኩል በሚፈጠረው የገበያ ትስስር ሲሆን ከዚህ ዘርፍ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሪ ግኝት ለማሳደግ ማዕድናትን በመምረጥ ግብይት መፈፀም እንዲሁም በዕደጥበብ እና ከልዩ አነስተኛ ማዕድን ማምረት ስራ ፈቀድ ጋር የተያያዙ የቴክኒክ ስራዎች ላይ በተቀጣሪነት የውጭ ዜጎችን ማሰተፍ የሚያስችል አሠራር በዚህ መመሪያ ውስጥ ማካተት በማስፈለጉ፤

በ.Ö መልኩ በዚህ ግብይት ላይ የሚሳተፉ የውጭ አገር ዜጎች ወደ ማዕድን ምርት ቦታ ሳይሄዱ ማዕድናትን በጥሬው ወይም በጌጥ መልክ ከተዘጋጀ በኋላ ወደ ውጭ ሀገር የመላክ ፈቀድ ካላቸው ባለፈቃዶች ጋር በመገናኘት የሚቀርበውን ማዕድን መለየትና መግዛት እንዲችሉና ከዚህ በፊት ወደ ማዕድን ምርት ቦታ የሚሄዱበትን አግባብ ማስቀረትና የግብይት ሥርዓቱ ሕግን መሰረት ባደረገ አግባብ እንዲቀጥል ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ማዕድናትን በጥሬው ወይም በጌጥ መልክ ከተዘጋጀ በኋላ ወደ ውጭ ሀገር ለመላክ ፈቀድ ያላቸው ባለፈቃዶችም በውጭ ሀገር ከሚገኙት የማዕድን ተረካቢዎቻቸው ጋር የገበያ ትስስር መፍጠር እንዲችሉ፣ ግብይቱን የሚፈጽሙ የውጭ ሀገር ዜጎችም ወደ ሀገር ውስጥ ሊገቡና ከባለፈቃዶች ጋር ሕግን መሰረት ባደረገ መልኩ መስራት እንዲችሉ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት፣ እንዲሁም ሕጋዊና ፍትሃዊ የግብይት ሥርዓት እንዲሰፍን ለማስቻልና የከበሩ ማዕድናት ወደ ውጭ ሀገር የመላክ ስራን ለማስተዳደር እንዲቻል በከበሩ ማዕድናት ግብይት አዋጅ ቁጥር 651/2001/ አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ይህ መመሪያ እንዲወጣ ተደርጓል።

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር
መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር
መዝገብ ቤት
RECORD
*Federal Democratic Republic of Ethiopia*
Ministry of Mines and Petroleum

## <u>ክፍል አንድ</u>
## <u>ጠቅላላ</u>

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ" የማዕድን ማምረት ስራ እና የከበሩ ጌጣጌጥ ማዕድናት ግብይት ስራ ላይ የውጭ ሀገር ዜጎች የሚሳተፉበትን አግባብ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ መመሪያ ውስጥ የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፤

1. የከበሩ ማዕድናት ግብይት አዋጅ ቁጥር 651/2001 ውስጥ የተዘረዘሩት ትርጓሜዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ።
2. "የውጭ ሀገር ዜጋ" ማለት ከማዕድን ላኪዎች እና ከእደጥበብ ስራ ባለፈቃዶች ማዕድን ለ[illegible]ግዛት ወይም ለእደጥበብና ለማዕድን ምርት ስራ ባለፈቃዶች በተቀጣሪነት የሙያ ስራ ለመስራት ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የኢትዮጲያ ዜግነት የሌላቸው ሰዎች ናቸው።
3. "ተቀጣሪ " ማለት ለዕደ ጥበብ ስራ ወይም ለምርት ሥራ ማምረቻ መሣሪያ አንቀሳቃሽነት ወይም የሙያ ስራ ለመስራት በባለፈቃዶች በቅጥር ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ የስራ ፈቃድ የተጠየቀለት የውጭ ሀገር ዜጋ ነው።
4. "ባለ ፈቃድ" ማለት የዕደ ጥበብ ስራና የልዩ አነስተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ስራ ፍቃድ የወሰደ ሰው ማለት ነው።
5. "የምስክር ወረቀት" ባለቤት ማለት ከበሩ ጌጣጌጥ ማዕድናትን በውጭ ገበያ ለማቅረብ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የላኪነት ብቃት ማረጋገጫ ሰርሰፍኬት የወሰደ ሰው ማለት ነው።
6. "ድጋፍ" ማለት በከበሩ ጌጣጌጥ ማዕድናት ባለፍቃድ ወይም በዕደ ጥበብ ባለፍቃድ ወይም የልዩ አነስተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ባለፍቃድ ጥያቄ መሠረት የውጭ ሀገር ዜጋው በቅጥር ወይም ለግብይት አላማ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባለት በሚኒስቴር መ/ቤቱ ለኢሚግሬሽንና ዜግነት መምሪያ ወይም ለሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚፃፍ ደብዳቤ ነው።
7. "ማዕድናትን ወደ ውጭ ሀገር የሚልኩ ሰዎች " ማለት በጥሬው ወይም በጌጥ የተሰራ የከበሩ ማዕድናትን ወደ ውጭ ሀገር የመላክ መብት ያላቸው የማዕድናት ላኪነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ወይም የዕደጥበብ ስራ ፈቃድ ባለቤቶች ናቸው።
8. "የማዕድን ማምርት ስራ" ማለት ልዩ የአነስተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ስራ ነው።

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በአዋጅ ቁጥር 651/2001 ወይም አዋጅ ቁ. 678/2002 ወይም አዋጅ.ቁ 816/2006 መሰረት ፤

1. ማዕድናትን በጥሬው ወይም በጌጥ መልክ ከተዘጋጀ በኋላ ወደ ውጭ ሀገር የመላክ መብት ባላቸው የላኪነት የምስክር ወረቀት ባሌቤቶች ከውጭ ሀገር የማዕድናት ገገርዎቻቸው ጋር በሚያደርጓቸው የግብይት ግንኙነቶች ላይ፣



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር
መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum

ማዕድናትን በጌጥ መልክ ከተዘጋጀ በኋላ ወደ ውጭ ሀገር የመላክ መብት ባላቸው የእደጥበብ ባለፈቃዶች ከውጭ ሀገር የማዕድናት ገገርዎቻቸው ጋር በሚያደርጓቸው የግብይት ግንኙነቶች ላይ፣

3. የማዕድን ማምረት ስራ ፈቃድ ባለቤት ሆነው የውጭ ሀገር ዜጋን በመቅጥር የሙያ ስራ ለማሰራት ለሚፈልጉ ባለፈቃዶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

<u>ክፍል ሁለት</u>

<u>በውጭ ሀገር ገቢያ ማዕድናትን ስለመሸጥና የውጭ ሀገር ዜጎች ተሳትፎ</u>

4. <u>በውጭ ሀገር ገበያ ማዕድናትን ስለመሸጥ</u>

1. በአዋጁ 651/2001 አንቀጽ 8 እና 11 መሰረት ማንኛው የእደጥበብ ፈቃድ ወይም የከበሩ ማዕድናት ላኪነት የምስክር ወረቀት ባለቤት የሆነ ሰው ማዕድናትን ወደ ውጭ ሀገር ልኮ መሸጥ ይችላል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ የተጠቀሰውን መብት ያለው ሰው ማዕድናቱን እራሱ ውጭ ሀገር በመውሰድ የመሸጥ ወይም ገገርዎች ወደ ሀገር ውስጥ ገብተው ማዕድናቱን እንዲገዙአቸው ማድረግ ይችላል።

3. በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ለውጭ ሀገር ዜጎች የማዕድናት ሽያጭ በብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሠረት ይከናወናል።

5. <u>የማዕድናት ግብይትና ምርት ላይ የሚደረግ ድጋፍ</u>

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ ቁጥር (2) መሰረት ማዕድናትን ለመግዛት ወይም ተቀጥረው የቴክኒክ ስራ ለማከናወን ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡ የውጭ ሀገር ዜጎች ድጋፍ እንዲደረግላቸው የሚፈልግ የእደጥበብ ባለፈቃድ ወይም የላኪነት ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ባለቤት ወይም የማዕድን ማምረት ስራ ባለፈቃድ ለሚኒስትር መስሪያ ቤቱ ማመልከቻ ማቅረብ አለበት።

6. ለማዕድን ግዢ ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገባ የውጭ ሀገር ዜጋ ድጋፍ የሚቀርብ ማመልከቻ ፣ ማዕድን ለመግዛት ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገባ የውጭ ሀገር ዜጋ ድጋፍ እንዲደረግለት የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፤

1. ድጋፍ የተጠየቀለትን የወጭ ሀገር ዜጋ፣

ሀ/ የፓስፖርቱን 2 ቅጂ እና የመኖሪያ አድራሻ የሚገልጽ ማስረጃ፣

ለ/ የሚገባበትን ዓላማ፣ የሚቆይበትን ጊዜ እና ግብይት ሊፈፅም ያቀደውን የማዕድናት ዓይነት፣

ሐ/ ማዕድኑን የሚሸጥበት ሀገር፣

2. የባለፈቃዱን ወይም የምስክር ወረቀት ባለቤቱን ፤

ሀ/ በዘመኑ የታደሰ ፈቃድ ወይም የላኪነት ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ዋናውን፣

ለ/ የዘመኑ ግብር መከፈሉን የሚገልጽ የገቢ ግብር ደረሰኝ፣

7. ለቴክኒክ ስራ ለመቀጠር ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገባ የውጭ ሀገር ዜጋ ድጋፍ የሚቀርብ ማመልከቻ

በዕደ ጥበብ ወይም በልዩ አነስተኛ ማዕድን ማምረት ባለፈቃድ በሰራተኝነት ለመቀጠር ወደ ሀገር ለሚገባ የውጭ ሀገር ዜጋ ድጋፍ እንዲደረግለት የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፤

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር መዝገብ ቤት RECORD Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Mines and Petroleum

፤ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባው የውጭ ሀገር ዜጋ፤

ሀ/ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ) የተዘረዘሩትን ማስረጃዎች፣

ለ/ የሚገባበትን ዓላማ፣ የሚቆይበትን ጊዜ እና እንዲሰማራበት የተፈለገው የስራ አይነት

ሐ/ የትምህርትና የስራ ልምድ ማስረጃ ፣

መ/ ጊዜው ያላለቀ የስራ ቪዛ

2. የባለፈቃዱን ፣

ሀ/ የታደሰ የዕደ ጥበብ ወይም የልዩ አነስተኛ ማዕድን ማምረት ስራ ፈቃድ፤

ለ/ ለስራ ሊቀጠር ወደ ሀገር ውስጥ ከሚገባው ሰው ጋር የተደረገ ስምምነት ዋናውን ከ 1 ቅጂ ጋር፣

ሐ/ የእውቀት ሽግግር ለማካሄድ ተተኪ ኢትዮጵያዊ የሚመድብ

መ/ ከዕዳ ነፃ መሆኑን የሚገልጽ መረጃ የሚያቀርብ

8. <u>የምስክር ወረቀት ባለቤት ግዴታ</u>

1. ማዕድን ለመግዛት ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ ድጋፍ የተጻፈለትን የውጭ ሀገር ዜጋ፣

ሀ/ ወደ ሀገር ውስጥ መግባቱን ወይም ሳይገባ መቅረቱን ፣

ለ/ ሀገር ውስጥ የሚቀይበት ጊዜ ሲጠናቀቅ ከሀገር መውጣቱን ፤

ሐ/ የገዛውን እና ወደ ውጭ የላከው የማዕድን መጠን፤

መ/ ለውጭ ዜጋው ለሽያጭ ያቀረበው ማዕድናት የገዛበት ሕጋዊ ምንጭ፣

ሠ/ ከማዕድናቱ ሽያጭ የተገኘውን የውጭ ምንዛሪ መጠን፣

ረ/ የማዕድናት ግብይት ስራን አቋርጦ በሌላ ተግባር የተሰማራ የውጭ ሀገር ዜጋ ካለ ዝርዝሩን ያካተተ ሪፖርት ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በየ 3 ወሩ ማቅረብ አለበት።

2. ማንኛው ላኪ በአንድ ጊዜ ከሦስት በላይ የውጭ ዜጎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ ድጋፍ መጠየቅ አይችልም። ተጨማሪ ሰዎች እንዲገቡ ጥያቄ ማቅረብ የሚቻለው መጀመሪያ ከገቡት የውጭ ዜጎች ተመልሰው ከሀገር በወጡት ሰዎች ቁጥር ልክ መሆን አለበት።

9. <u>የባለፈቃዶች ግዴታ</u>

1. የዕደጥበብ ወይም የማዕድን ማምረት ስራ ባለፈቃዶች በቴክኒክ ሰራተኝነት ለመቅጠር ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ ድጋፍ የጠየቁለት የውጭ ሀገር ዜጋ፣

ሀ/ ወደ ሀገር ውስጥ መግባቱን ወይም ሳይገባ መቅረቱን ፣

ለ/ ሀገር ውስጥ የሚቀይበት ጊዜ ሲጠናቀቅ ከሀገር መውጣቱን ፤

ሐ/ የማዕድን ቴክኒክ ስራውን አቋርጦ በሌላ ተግባር የተሰማራ የውጭ ሀገር ዜጋ ካለ ዝርዝሩን ያካተተ ሪፖርት ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በየ 3 ወሩ ማቅረብ አለበት።

2. ማንኛው ባለፈቃድ በአንድ ጊዜ ከሦስት በላይ የውጭ ዜጎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ ድጋፍ መጠየቅ አይችልም። ተጨማሪ የውጭ ዜጎች እንዲገቡ ጥያቄ ማቅረብ የሚቻለው መጀመሪያ ከገቡት የውጭ ዜጎች ተመልሰው ከሀገር በወጡት ሰዎች ቁጥር ልክ መሆን አለበት።



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር
መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum

ዐ. ለቅጥር ወይም ለማዕድናት ግዢ የገቡ የውጭ ሀገር ዜጎች ግዴታ

ለከበሩ ማዕድናት ግብይት ስራ ወይም ለልዩ አነስተኛ ማዕድን ማምረት ስራ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ የውጭ ሀገር ዜጎች የሚከተሉትን ግዴታዎች ማክበር አለባቸው ::

1. የማዕድናት ግዢ ለመፈፀም የሚገቡ ሰዎች ሲሆን፤

ሀ/ የማዕድናት ግዥ በላኪው ወይም በዕደጥበብ ባለፈቃድ በተፈቀደለት ቢሮው ወይም መጋዘን ብቻ መፈፀም ::

ለ/ ማዕድናት የሚመረቱበት ቦታ አለመሄድ ::
ሐ/ ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ ለመግዛት የተስማሙበትን ማዕድን የመግዛት ፤
መ/ ከእደጥበብ ባለፈቃድ ወይም ላኪ ብቻ የማዕድናት ግዢ መፈፀም፤
ሠ/ ለኢትዮጵያ ዜጎች የእውቀት ሽግግር ማግኘት በሚያስችል መልኩ ስራቸውን ማከናወን፤

2. በማዕድናት ምርት ወይም እደጥበብ ቴክኒክ ስራ ላይ ለተቀጠሩ ተቀጣሪ ሲሆን፤

ሀ/ለመስራት ተስማምተው ወደ ሀገር ውስጥ የገቡትን የማዕድን ምርት ወይም የእደጥበብ ቴክኒክ ስራ ላይ ብቻ የመስራት፤

ለ/ ለኢትዮጲያዊ ዜጎች የእውቀት ሽግግር መፈፀም ባለበት አሰራር ብቻ ስራቸውን ማከናወን፤

3. ማንኛውም በማዕድን ስራ ላይ ለመሰማራት ወደ ሀገር ውስጥ የገባ የውጭ ሀገር ዜጋ ተጨማሪ የቆይታ ጊዜ እንዲያገኝ ድጋፍ ካልተጻፈለት በስተቀር የተፈቀደለት ጊዜ ሲጠናቀቅ ወደ መጣበት ይመለሳል፤

11. የውጭ ዜጎችን የቆይታ ጊዜ ስለማራዘም

ለልዩ አነስተኛ ማዕድን ማምረት ሥራ ወይም ለቴክኖሎጂና ዕውቀት ሽግግር በባለፈቃዶች የተቀጠረው የውጭ ሀገር ዜጋ ለተጨማሪ ጊዜያት እንዲቆይ ጥያቄ ሲቀርብ ቆይታው አገባብ ባለው ሕግ የሚወሰን ሆኖ በሚኒስቴሩ የሥራው ሪፖርት ተገምግሞ ለተወሰኑ ተጨማሪ ጊዜያት እንዲቆይ የድጋፍ ደብዳቤ ሊጻፍለት ይችላል።

## ክፍል ሶስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

12. የተከለከሉ ተግባራት

1. ማንኛውም ባለፈቃድ በቱሪስት፤ በኢንቨስትመንት፤ ወይም ለማዕድናት ግብይት ላልሆነ ለማናቸውም ዓላማ ከገቡ የውጭ ሀገር ዜጎች ጋር ጥሬ ማዕድናት (ዕሴት ያልተጨመረበት) የማዕድናት ግብይት ማከናወን አይችልም።
2. ማንኛውም ላኪ ለግብይት ዓላማ ወደ ሀገር ውስጥ የገባውን የውጭ ሀገር ዜጋ ወደ ክልል ይዞ በመሄድ በምርት ቦታና አካባቢ፤ በሆቴሎችና በፈቃዱ ከተመለከተው የስራ ቦታ ውጭ ግብይት ማከናወን አይችልም።



የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር
መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum

3. ማንኛውም በዚህ መመሪያ መሰረት ወደ ሀገር ውስጥ የገባ የውጭ ሀገር ዜጋ ሊሰራው ከመጣበት ስራ ውጭ የስራ መስኮች መሠማራት አይችልም።

4. ማንኛውም ላኪ ወይም የዕደ ጥበብ ባለፈቃድ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የድጋፍ ደብዳቤ ሳያገኝ የውጭ ዜጎችን በቅጥርና ለግብይት ዓላማ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት አይችልም።

## 13. <u>ቅጣት</u>

ማንኛውም ባለፈቃድ ወይም ላኪ በዚህ መመሪያ የተከለከሉ ተግባራትን ፈጽሞ ሲገኝ በከበሩ ማዕድናት ግብይት አዋጅ ቁጥር 651/2001 ወይም እንደሁኔታው የማዕድን ስራዎች አዋጅ ቁጥር 678/2002 መሰረት በማድረግ በወጣው ደንብ የተዘረዘሩት ቅጣቶች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

ይህ መመሪያ ከ ........../ 2010 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።

አዲስ አበባ መስከረም ........ቀን 2010 ዓ.ም

ቴዎድሮስ ገ/እግዚያብሔር

የማዕድን፣ የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚኒስቴር

ሚኒስትር ዴኤታ

መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum